# የሜሪላንድ የጤናና የአእምሮ ሀይጂን መምርያ
# እና የጤናዎ መረጃ

## የምስጢር አሰራር ማስታወቂያ

**ይህ ማስታወቂያ ስለየርስዎ የጤና መረጃ አጠቃቀም እና ለሌላ ማሳወቅ እናም እርስዎ ይህን መረጃ እንዴት ሊደርሱበት እንደሚችሉ ይገልፃል። እባክዎ በጥንቃቄ ደጋግመው ይመልከቱት።**

**<u>መግቢያ</u>**

የሜሪላንድ የጤናና የአእምሮ ሀይጂን መምርያ/Maryland Department of Health and Mental Hygiene/ (DHMH) የጤናዎን መረጃ ለመጠበቅ ግዴታ ገብቷል። DHMH የተጠበቀ የጤና መረጃ/Protected Health Information/ (PHI)ን እንዲንከባከብ በህግ ይጠበቅበታል። PHI የሚያካትተው ከርስዎ አካላዊ ወይም የአእምሮ ጤና ጋር የተያያዘ ከርስዎ ወይም ከሌላ ያገኘነው ማንኛውንም ለመለየት የሚቻል መረጃ፣ የተቀበሉት የጤና እንክብካቤ፣ ወይም ለጤና የተደረገ ክፍያ ነው። ህጉ በሚጠይቀው መሰረት፣ የPHIን ምስጢራዊነት በሚመለከት ይህ ማስታወቂያ ስለ ሙብቶችዎና የኛ ህጋዊ ተግባሮችና የምስጢር ልምዶች መረጃ ይሰጥዎታል። ህክምና ለመስጠት ወይም ለጤናዎ እንክብካቤ ለማስከፈል፣ DHMH የተወሰኑ የጤና መረጃዎችን ይጠይቃል እናም ያ የጤና መረጃ (መ)ማህደርዎ ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል። ይህ ዘገባ በአብዛኛው የርስዎን ህመም ምልክቶች፣ የምርመራና የፈተና ውጤቶች፣ የምርምር ትንተናዎች፣ እና ህክምናን ይይዛል። ያ መረጃ፣ የርስዎ ጤና ወይም የህክምና ዘገባ ተብሎ የሚጠቀስ፣ እናም በህግ የጤና መረጃ ሆኖ የሚጠበቅ፣ ለተለያዩ ተግባሮች አገልግሎት ሊውል ይችላል።

ምንም እንኳን DHMH የኛን ምስጢራውነት ልምዶችና የዚህን ማስታወቂያ ሃሳቦች/መርሆዎች በማንኛውም ጊዜ የመለወጥ ሙብቱን የሚጠብቅ ቢሆንም፣ DHMH እና የቢዝነስ አቻዎቹ በዚህ ማስታወቂያ ላይ የተገለፁትን የምስጢራዊነት ልምዶች መከተል ይጠበቅባቸዋል። የአዲሱን ማስታወቂያ ቅጂ ከማንኛውም የDHMH ወኪል መጠየቅ ይችላሉ። በ(ድርጣብያችን)ድረገጻችን በhttp://dhmh.maryland.govም በተጨማሪ ተለጥፎ ይገኛል።

**<u>ተፈላጊ አጠቃቀሞችና መገለጫዎች</u>**

የDHMH ሰራተኞች የርስዎን መረጃ የሚጠቀሙበት ስራቸውን ሲሰሩ ብቻ ነው። DHMH በዘል(ም)ማድ ከሚያከናውነው ባሻገር ለመልገያ ለመዋል፣ ህጉ የሚፈቅደው ወይም የሚጠይቀው ካልሆነ በስተቀር፣ DHMH የርስዎ የፅሁፍ ፈቃድ የግድ ያስፈልገዋል፣ ከተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች በስተቀር እንደዚህ ያለውን ፈቃድ ማንሳት ይችላሉ። የሚከተሉት የርስዎ የጤና መረጃ ተፈላጊ አጠቃቀሞችና መገለጫዎች ከምንላቸው የተ(ው)ወሰኑ ናሙናዎች ናቸው፡-

**ህክምና፣ ክፍያ፣ ወይም የጤና እንክብካቤ ግብረቶችን በሚመለከት ያለፈቃድ የሚከናወኑ ተፈላጊ አጠቃቀሞችና መገለጫዎች፡-**

- **<u>ለህክምና</u>**፡- DHMH ህክምና ለማፅደቅ፣ ለመከልከል፣ የመድሃኒት ህክምናዎ ተገቢ መሆኑን ለመወሰን በጤና መረጃዎ ለመገልገል ወይም ለመጋራት ሊጠቀምበት ይችላል። ለምሳሌ፣ የDHMH የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ለህክምና ጉዳይ ወይም እንክብካቤ ለማቀነባበር የጤና መረጃዎን ከግል ሀኪምዎ ጋር አብሮ መገምገም ሊያስፈልጋቸው ይችላል።
- **<u>ክፍያ ለማግኘት</u>**፡- ለጤናዎ እንክብካቤዎች ክፍያ ለመሰብሰብ ቢል (ማስከፈያ) ለማዘጋጀት እና በአ(ግ)ገልግሎቶቻችን ለመሳተፍ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን DHMH በጤና መረጃዎ ለመገልገል ወይም ለመጋራት ሊጠቀምበት ይችላል። ለምሳሌ፣ የጤና አቅራቢዎ ለርስዎ ለቀረቡ የሕክምና አገልግሎቶች ይገባኛሎች መላክ ይችላል።
- **<u>ለጤና አጠባበቅ ግብረቶች</u>**፡- DHMH የአገል(ጎ)ግሎቶችን ጥራት ለመገምገም፣ ወይም ለስቴታችን ወይም ለፌደራላዊ ኦዲተሮች፣ በጤናዎ መረጃ መገልገል ወይም መጋራት ይችላል።

**ሌሎች በህግ የሚጠየቁ ወይም የተፈቀዱ የጤና መረጃ አጠቃቀሞችና መገለጫዎች፡-**

- **<u>ለመግለጫ/ማሳሰብያ ጉዳዮች</u>**፡- አማራጭ መንገዶች ካልሰጡን በስተቀር፣ DHMH ስለፕሮግራሙ የቀጠሮ ማስታወሻዎችና ሌሎች ቁሳቁሶች ወደቤትዎ ሊልክ ይችላል።
- **<u>በህግ ሲፈለግ</u>**፡- በህግ ሲፈለግ DHMH የጤና መረጃን ሊያሳይ ይችላል።
- **<u>የህዝብ ጤና እንቅስቃሴዎች</u>**፡- DHMH ህመሞችን፣ ጉዳቶችን የሚመለከት መረጃ መሰብሰብ ወይም ዘገባ ማቅረብ ሲፈለገበት ወይም ወሳኝ ስታቲስቲኮች በመምርያው ውስጥ ለሌሎች ክፍሎች ወይም የህዝብ ጤና ባለስልጣኖች ዘገባ ማቅረብ ሲፈለግበት DHMH የጤና መ(ር)ረጃዎችን መግለፅ ይችላል።
- **<u>የጤና ቁጥጥር እንቅስቃሴዎች</u>**፡- በህግ ለሚፈለጉ የቁጥጥር ተግባሮች የርስዎን የጤና መረጃ ለሌሎች መምርያው ውስጥ ለሚገኙ ክፍሎች ወይም ሌሎች ወኪሎች DHMH ማሰራጨት ይችላል። የነዚህ የቁጥጥር እንቅስቃሴዎች ናሙናዎች የኦዲት ስራዎች፣ ፍተሻዎች፣ ምርመራዎች እና የስራ ፈቃድ አሰጣጥ ናቸው።
- **<u>የሬሳ መርማሪዎች፣ የህክምና መርማሪዎች፣ የቀብር ስነስርአት ስራ አስኪያጆች እና የአካል ስጦታዎች</u>**፡- DHMH ለሬሳ መርማሪዎች፣ ለህክምና መርማሪዎች ወይም ለቀብር ስነስርአት ስራ አስኪያጆች፣ እና ከሰውነት አካል፣ አይን፣ ወይም የስጋ ስጦታዎች የአካል ቁራጭ ዝውውሮች ጋር ለተያያዙ የተፈቀደላቸው ድርጅቶች የጤና መረጃ መግለጽ(ፅ) ይችላል።
- **<u>ለምርመራ ስራዎች</u>**፡- በተወሰኑ ሁኔታዎች፣ በInstitutional Review Board (የተቋማዊ ግምገማ ቦርድ) ወይም በሌላ የተሰየመ የሚስጢራዊ ቦርድ ቁጥጥር ስር፣ የህክምና ምርምርን ለመደገፍ DHMH የጤና መረጃ ሊገልፅ ይችላል።
- **<u>ለጤና ወይም ደህንነት አደጋ ለመከላከል</u>**፡- ለጤና ወይም ለደህንነት ከፍተኛ አደጋ ለማስወገድ፣ ለህግ አስከባሪዎች ወይም የጉዳት አደጋ ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ለሚችሉ ሌሎች ግለሰቦች DHMH የጤና መረጃ እንዳስፈላጊነቱ መግለፅ ይችላል።
- **<u>አመፅ እና ቸልታ</u>**፡- የአመፅ፣ የቸልታ፣ የቤት ውስጥ ሁከት፣ ወይም የሌላ ወንጀል ሰለባ ይሆናሉ ብለን ማሰብ ከቻልን DHMH የጤናዎን መረጃ አግባብ ላላቸው ባለስልጣኖች ይገልፃል። ለጤናዎ ወይም ደህንነትዎ ወይም የሌሎች ጤና ወይም ደህንነት ለማስወገድ አስፈ(ለ)ላጊ እስከሆነ ድረስ DHMH የጤናዎን መረጃ ይገልፃል።

- ***ልዩ የመንግስት ተግባሮች***:- በተወሰነ ሁኔታ የሚገኙ የሚሊታሪ አባሎችንና አርበኞች፣ በተወሰነ ሁኔታ የሚገኙ የጠባይ ማረሚያ አገልግሎቶች፣ ከብቃትና ከምዝገባ ጋር የተያያዙ የመንግስት ፕሮግራሞች፣ እንደ የፕረዚደንቱ ጥበቃ ለመሰሉ የብሄራዊ ደህንነት ምክንያቶች DHMH የጤና መረጃቸውን መግለፅ ይችላል።
- ***በርስዎ እንክብካቤ የሚሳተፉ ዘመዶች፣ ጓደኞች፣ ወይም ሌሎች***:- ከእንክብካቤዎ ወይም ከእንክብካቤዎ ክፍያ ጋር በቀጥታ ከሚገናኙ ግለሰቦች ጋር DHMH የጤናዎን መረጃ መጋራት ይችላል። በተጨማሪ ስለ አድራሻዎ፣ ስለአጠቃላይ ሁኔታዎ፣ ወይም ስለሞትዎ የጤናዎን መረጃ DHMH ከሰዎች ጋር መጋራት ይችላል።
- ***የ(ስ)ሰራተኛ ካሳ***:- ከስራ ጋር ለተያያዙ ጉዳቶች ወይም በሽታዎች፣ አጥፊው የፈለገውን ይሁን፣ ጥቅሞች ለሚያቀርቡ የሰራተኛ መካካሻ ፕሮግራሞች DHMH የጤና መረጃ መግለፅ ይችላል።
- ***የህመምተኛ ማውጫዎች***:- DHMH በአብዛኛው ጊዜ በስምዎ ለሚጠሩ ለቴሌፎን ጠያቂዎችና ጎብኝዎች ማውጫዎች አይዙም። ስለሆነም፣ አንድ የDHMH አካል ማውጫ ቢይዝም፣ ላልታወቀ ቴሌፎን ደዋይ ወይም ጎብኚ ያለፈቃድ ማንነትዎ አይነገረውም/አይ(ን)ነገራትም፣ የሚገለፀውም የተወሰነ መረጃ ስምዎን፣ የሚገኙበትን ክፍል፣ አጠቃላይ ሁኔታዎን (ለምሳሌ፣ ደህና፣ ጽኑ, ወዘተ.) እና ሃይማኖትዎን ሊይዝ ይችላል።
- ***ክሶች፣ ክርክሮች እና የይገባኛል ጥያቄዎች***:- በፍርድ ቤት ክስ፣ ክርክር፣ ወይም የይገባኛል ጥያቄ ተጠምደው ከሆነ፣ በፍርድ ቤት ወይም የአስተዳደር ትእዛዝ፣ መጥሪያ፣ የምርመራ ጥያቄ፣ በርስዎ ስም ለተከፈትው የቅሬታ ፋይል ምርመራ፣ ወይም ሌላ ህጋዊ ሂደት DHMH የጤናዎን መረጃ ሊገልፅ ይችላል።
- ***የህግ ማስከበርያ***:- በህግ ለሚፈለጉ ወይም ለፍ/ቤት መጥርያ መስረት ምላሽ DHMH የጤናዎን መረጃ ለህግ አስከባሪ መግለፅ ይችላል።
- ***የተፈቀዱ ስራዎችን ለሚያከናውኑ ሌሎች ወገኖች***:- እላይ የተገለፁትን ተግባሮች DHMH ራሳችን ማከናወን፣ ወይም DHMH-ባልሆኑ ድርጅቶች (የቢዝነስ ሽርካዎች ተብለው የሚታወቁ) እነዚያን ተግባሮች እንዲፈፅሙ መገልገል እንችላለን። እኛን እንዲተኩ የርስዎን PHI ለሶስተኛ ወገን በምንሰጥባቸው ወቅቶች፣ በልዩ የምስጢራዊነት ውል አማካይነት የርስዎን PHI እንጠብቃለን።
- ***የገንዘብ መዋጮ ስራዎች***:- ለDHMHና ለግብረቶቹ ገንዘብ ለመሰብሰብ እርስዎን እንዲገ(ን)ኙ የርስዎን መረጃ DHMH ሊጠቅምበት ይችላል። ይፋ የምናደርገው መረጃ ስለርስዎ መገናኛ፡ ስምዎን፣ አድራሻና ቴሌፎን ቁጥር እና የታከሙበት ወይም አገልግሎት DHMH የተቀበሉበት ቀኖች የመሰሉ፣ ብቻ ይሆናሉ።

## ***መብቶችዎ***

***ያለዎት መብት***:-

- ***ገደብ መጠየቅ***:- DHMH ከጤናዎ መረጃ የሚጠቀምበትንና የሚያጋልጠውን ገደብ (ኢ)እንዲደረግበት የመጠየቅ መብት አለዎት። DHMH ጥያቄውን እስከተቻለ ያስተናግዳል፣ ነገር ግን ከገደብ ጥያቄው ጋር እንዲስማማ በህግ አይፈለግበትም። በአንፃሩ በህግ ካልተጠየቀ በስተቀር፣ ገለፃው ክፍያ ለማከናወን ወይም ለጤና እንክብካቤ ግብረቶች (እና ህክምና ለማከናወን ካልሆነ) የጤና ፕላን እስከሆነ ድረስ DHMH ጥያቄዎን ማስተናገድ አለበት፤ እናም (የሚጠበቀው) የጤና መረጃ ለሚመለከተው የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ሙሉ በሙሉ ከኪስ የተከፈለበት ለአንድ የጤና እንክብካቤ ነገር ወይም አገልግሎት ብቻ የሚመለከት ከሆነ።
- ***የምስጢር መገናኛ መጠየቅ***:- DHMH መረጃዎች በተለዋጭ አድራሻ ወይም በተለዋጭ ዘዴ እንዲልክልዎ የመጠየቅ መብት አለዎት። ይህን ለመፈፀም ተቀባይነት ባለው መንገድ (ቅ)ቀላል ሆኖ እስካገኘነው ድረስ DHMH በጥያቄዎ መስማማት አለበት።
- ***መፈተሽና ቅጂ ማድረግ***:- ከአንዳንድ (ውጭ የሆኑ) ነገሮች (exceptions) በስተቀር (እንደ የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎች፣ ለተወሰኑ የህግ ሂደቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች፣ እና በህግ የተወሰነ/የተጠበቀ የጤና መረጃ)፣ በፅሁፍ ሲጠይቁ የጤናዎን መረጃ ማየት ይችላሉ። የጤናዎ ቅጅዎች ካስፈለገዎ፣ በወጪ የተመሰረተ የፎቶ-ኮፒ፣ የፖስታ፣ እና የተጠበቀው የጤና መረጃ መግለጫ ወይም ማጠቃለያ ተቀባይነት ያለው ክፍያ ሊጠየቁ ይችላሉ። ከመረጃዎ ቅጂ የሚደረግላቸውን ክፍሎች የመምረጥና የቅጂ ዋጋ በቅድሚያ መረጃ የማግኘት መብት አለዎት። DHMH የርስዎን የጤና መረጃ በኤሌክትሮኒክ የጤና ዘገባ ይይዘዋል፣ በኤሌክትሮኒክ ቅርፀት በኩል መዳረሻ እናቀርባለን እናም፣ የዚህ አይነቱ ምርጫ ግልፅ፣ የሚታይ፣ እና የተወሰነ እስከሆነ ድረስ፣ እርስዎ ለሰየሙት አቋም ወይም ግለሰብ የጤና መረጃውን እናስተላልፋለን።
- ***ማሻሻያ/ለውጥ መጠየቅ***:- የጤናዎን ዘገባ እንዲያርም ወይም እንዲጨምርበት DHMHን በፅሁፍ መ(ጥ)ጠየቅ ይችላሉ። DHMH ለጥያቄዎ በ60 ቀኖች ውስጥ መልስ ይሰጣል፣ ካስፈለገ፣ በተጨማሪ 30-ቀን ውስጥ። DHMH የጤናዎን መረጃ:- (1) ትክክለኛና የተሟላ፤ (2) በኛ ያልተፈጠረ እና/ወይም የዘገባዎቻችን አካል ሆኖ ካልተገኘ፤ (3) እንዲገለፅ ያልተፈቀደ ሆኖ ካገኘው፣ DHMH ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል። DHMH የማሻሻያውን ጥያቄ ካፀደቀው፣ DHMH የጤና መረጃውን ይለውጥና ያስታውቅዎታል፤ እናም DHMH በጤና መረጃው ስለተደ(ር)ረገው ለውጥ ማወቅ ለሚያስፈልጋቸው ሌሎችም ይነግራቸዋል።
- ***ፈቃድ ለመስጠት መጠየቅ*** :- ለአብዛኛዎቹ መገልገያዎች እና የሳይኮቴራፒ ማስታወሻ የመገለፅ ሁኔታ፣ የሽያጭ ማስታወቂያ ለመቀበል እና ስለ የርስዎ PHI ሽያጭ የርስዎ ፈቃድ እንዲኖር የመጠየቅ መብት አለዎት።
- ***የመረጃ መግለጫዎች ዘገባ መቀበል***:- ከኤፕረል14 2003 ጀምሮ እና ሂሳቡ ከተጠየ(ቅ)ቀበት በፊት በሚገኙት ስድስት ወራቶች ውስጥ የርስዎ የጤና መረጃዎች የተገለፁባቸውን ዝርዝር የመጠየቅ መብት አለዎት። ከዚህ ውጭ የሚሆኑት ለህክምና፣ ለክፍያ፣ እና ለጤና እንክብካቤ ግብረቶች አገልግሎት ላይ የዋሉ የጤና መረጃዎች ናቸው። በተጨማሪ፣ ለብሄራዊ ደህንነት፣ ለህግ (እ)አስከባሪ መኮንኖች፣ ወይም ለጠባይ ማረምያ ተቋሞች የተሰጡትን፣ በፅሁፍ በስጡት ፈቃድ መሰረት፣ DHMH ለርስዎ የተደረጉትን ገለፃዎች መዘርዘር የለበትም። በአመት እስከ አንድ ተመሳሳይ ጥያቄ ድረስ ክፍያ አይጠየቅበትም። በተጨማሪ፣ DHMH ለህክምና፣ ለክፍያ፣ እና ለጤና እንክብካቤ ግብረቶች በኤሌክትሮኒክ የጤና ዘገባ አማካይነት የመግላጫዎች ሂሳብ ያቀርባል፣ ነገር ግን መረጃው ከተጠየቀበት ላለፉት ሶስት አመቶች ብቻ የተወሰነ ነው።
- ***የመውጣት/የመሰረዝ ምርጫ***:- የገንዘብ መዋጮ መገናኛ/ማስታወቂያ የመቀበል እና ከገንዘብ መዋጮ መገናኛ ለመውጣት የመጠየቅ መብት አለዎት። ከDHMH አገልግሎት የህመምተኛ ማውጫ ለመሰረዝ የመጠየቅ መብትም አለዎት።
- ***ማስታወቂያ መቀበል***:- የዚህ ማስታወቂያ የወረቀት ቅጂ እና/ወይም የኤሌክትሮኒክ ቅጂ ሲጠይቁ በፖስታ የመቀበል መብት አለዎት።
- ***የመጣስ ማስታወቂያ መቀበል***:- የርስዎ ያልተጠበቀ PHI መደፈር ሲያጋጥም ማስታወቂያ የመቀበል መብት አለዎት።
- ***የፆታ መረጃ ጥበቃ መቀበል***:- ከDHMH የጤና እንክብካቤ አካሎች አንዱ የጤና ፕላን ተብሎ ከታሰበ፣ የጤና ፕላኑ በርስዎ ፆታዊ መረጃ የመጠቀም ወይም ለተወ(ስ)ሰኑ የዋስትና ጉዳዮን ከመግለፅ የተከለከለ ነው።

- **<u>የአእምሮ ጤና ዘገባዎች ጥበቃ መቀበል</u>፡-** የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ከመቀበልዎ ጋር ተያይዞ የዳበረ የህክምና ዘገባ ካለርስዎ ፈቃድ ተጋልጦ ከሆነ፣ DHMH ገለፃ ካስፈለገበት አላማ ጋር አስፈላጊ የሆነውን ከማህደርዎ የሚገኘውን መረጃ ብቻ ይፋ ያደርጋል።

**ለተጨማሪ መረጃ፡-**
ይህ ሰነድ የAmericans with Disabilities Act (ስንክልና ያላቸው አሜሪካውያን አዋጅ) መመርያዎች በሚያሟሉ ሌሎች ቋንቋዎችና ተለዋጭ ቅርጸቶች ይገኛል። ጥያቄዎች ካለዎትና ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ **(የተሰየመ የቢዝነስ ጓድ የምስጢራዊነት መገናኛ ቁጥር ያስገቡ/Insert Designated Business Unit Privacy Contact Name and Number)**___________________________________________________ መገናኘት ይችላሉ።

**ስለየምስጢራዊነት አፈፃፀማችን ስሞታ ለማቅረብ፡-**
የምስጢራዊነት መብቶችዎ ተደፍረዋል ብለው ያ(ም)ምኑ እንደሆነ፣ ቅሬታ ማስመዝገብ ይችላሉ።
- በጤናና የአእምሮ ሀይጂን፣ ኮርፖሬት ኮምፕላያንስ ክፍል (Department of Health and Mental Hygiene, Division of Corporate Compliance)፣ በ1-866-770-7175 ቅሬታ ማስመዝገብ ይችላሉ።
- ለዩ.ኤስ. የጤናንና ህዝባዊ አገልግሎቶች መምርያ ጸሀፊ፣ የሲቪል መብቶች ፅ/ቤት (Secretary of the U.S. Department of Health and Human Services, Office of Civil Rights) ቅሬታ ማስመዝገብ ይችላሉ። ለመገናኛ መረጃ የጤናንና ህዝባዊ አገልግሎቶች መምርያን መጠየቅ ይችላሉ።

የዚህ አይነት ቅሬታ ቢያሰሙ DHMH በርስዎ ላይ የአፀፋ እርምጃ አይወስድብዎትም።
**ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን፡-** ይህ ማስታወቂያ ከኦገስት 19 2013 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

---

**(የአቅራቢ ፕሮግራሞች ይህ ማረጋገጫ መፈረሙን ማረጋገጥ አለባቸው)**
የዚህ ማስታወቂያ መቀበል ማረጋገጫ

________________________________ ____________________
ሕመምተኛ ወይም ህጋዊ ወኪል ፊርማ ቀን

ለማረጋገጥ ካልቻሉ፣ ለምን እንደሆን ያብራሩ፡-

________________________________________
የDHMH ተወካይ ፊርማ